# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች

# ደህና ሰንብት ፈርዖን!




ጸሐፊው: Edward Hughes
ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest
የተተረጎመው: Abel Eshetu
ያሻሽለው (አሻሽሎ የጻፈው): Lyn Doerksen


ታሪክ 11 ከ 60 ዎቹ መሃከል


www.M1914.org

**Bible for Children,** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*



ፈቃድ፦ ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።


አማርኛ

Amharic



ፈርዖን በጣም ተቆጣ!
ባሪያ ያደረጋቸውን
እስራኤላውያንን
እንዲለቃቸው እግዚአብሔር
በሙሴ በኩል አዘዞት
ነበር፤ ፈርዖን ግን
እምቢ አለ።

1



ፈርዖን አስገባሪዎቹን
“ስራ እያበዛችሁ
እስራኤላውያንን
አስጨንቋቸው።”
አላቸው። ስለሆነም
ኑሮ ለእስራኤላውያን
እጅግ ከፋባቸው።

2


ፈርዖንም “ሂዱ፥ ሥሩ ገለባ አይሰጡአችሁም፥ የሚፈለግባችሁን የጡቡን ቊጥር ግን ታመጣላችሁ አላቸው።” ትዕዛዙም ጠንካራ ነበር።
3
የፈርዖንም አስገባሪዎች፦ ቀድሞ ታደርጉ እንደ ነበራችሁ ትናንትትናና ዛሬ የተመደበላችሁን ጡብ ስለ ምን አትጨርሱም? እያሉ በእስራኤል ልጆች ላይ
የተሾሙትን አለቆቹን ገረፉ።
4
ሕዝቡም መከራ ያመጣችሁብን እናንተ ናችሁ ብለው ሙሴንና አሮንን አማረሩ። ሙሴም ወደ እግዚአብሔር ፀለየና። ጌታ ሆይ፥ አንተም ሕዝብህን ከቶ አላዳንኸውም አለ።
እግዚአብሔርም፦እኔ እግዚአብሔር ነኝ፥ ከግብፃውያንም ባርነት አወጣችኋለሁ ብሎ መለሰ።
5
እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን እንደገና ወደ ፈርዖን ላካቸው። ፈርዖንም፦ ተአምራትን አሳዩኝ ሲላቸው፥አሮን በትሩን በፈርዖንና በባሮቹ ፊት ጣለ፥ እባብም ሆነች።
6
ፈርዖንም ጠቢባንንና መተተኞችን ጠራ የግብፅም ጠንቋዮች በአስማታቸው እንዲሁ ደግሞ አደረጉ። እያንዳንዳቸውም በትራቸውን ጣሉ፥ እባቦችም ሆኑ የአሮን በትር ግን በትራቸውን ዋጠች።
7
በነገታው ሙሴና አሮን ፈርዖንን ወንዝ ዳር አገኙት። አሮንም በትሩንም አነሣ፥ በፈርዖንና በባሪያዎቹም ፊት የወንዙን ውኃ መታ የወንዙም ውኃ ሁሉ ተለውጠ ደም ሆነ። ዓሦች ሞቱ ወንዙም ገማ፥
ግብፃውያንም ከወንዙ ውኃ መጠጣት አልቻሉም።
8


ነገር ግን ፈርዖን ልቡን አደነደነ። ሕዝቡንም ለመልቀቅ እንቢ አለ።
9


ሙሴ ፈርዖንን “ሕዝቡን ልቀቅ” ብሎ እንደገና ተናገረው። እግዚአብሔር ሌላ መቅሰፍት ላከበት። ጓጉንቸሮችም ወጥተው ወደ ቤት፥ ወደ መኝታ ቤት፥ ወደ አልጋህ፥ ወደ ምድጀች፥ ወደ ቡሃቃዎችም ገቡ።
10


ፈርዖንም ጓጉንቸሮቹን እንዲያርቅልን ወደ እግዚአብሔር ጸልዩልኝ፤ ሕዝቡን እለቅቃለሁ አላቸው። ጓጉንቸሮቹ ሲወገዱ ፈርዖንም መልሶ ልቡን አደነደነ።
11


አሮንም እጁን ዘረጋ፥ በበትሩም የምድሩን ትቢያ መታው፥ በሰውና በእንስሳም ላይ ቅማል ሆነ። የፈርዖን ልብ ግን ደነደነ።
12


ቀጥሎም እግዚአብሔር የዝንብ መንጎች፤ ሰውንና ከብቶቹን የገደለ ብርቱ ቸነፈር፤በሰውና በእንስሳም ላይ ቍስል ላከባቸው። ፈርዖን ግን አሁንም ልቡን አደነደነ። ሕዝቡን አለቅም አለ።
13


ከዚያም አንበጣዎች በአገሩ ሁሉ ላይ ወጡ። የአገሪቱን ቡቃያ ሁሉ  በዛፉ የነበረውን ፍሬ ሁሉ፤ ለምለም ነገር ዛፍም የምድር ሣርም ሁሉ በሉ።
14


ከዚያም ሙሴ እጁን ወደ ሰማይ ዘረጋ፥ በግብፅም አገር ሁሉ ላይ ፅኑ ጨለማ ሦስት ቀን ሆነ። ይሁንና ፈርዖን እስራኤላውያንን ሊለቅቃቸው አልፈቀደም።
15


እግዚአብሔርም ሙሴን፦በግብፅ ላይ ገና አንዲት መቅሰፍት አመጣለሁ አለ። ከፈርዖን በኵር ጀምሮ ወፍጮ ፈጭ እስከሆነችው እስከ ባሪያይቱ በኵር ድረስ፥ የከብቱም በኵር ሁሉ ይሞታል አለው። እንደዚያም ሆነ እስራኤላውያን የበራቸውን መቃን በበግ ደም ስለቀቡት በኩራቸው አልሞተም።
16


በሌሊትም በግብጽ ምድር ታላቅ ለቅሶ ሆነ። በእያንዳንዱ ቤት ቢያንስ አንድ ሰው ሞቷል።
17


ፈርዖንም ሙሴንና አሮንን በሌሊት ጠርቶ፡- እናንተ የእስራኤል ልጆች ተነሡ፥ ከሕዝቤ መካከል ውጡ ሂዱም፥ እንዳላችሁም እግዚአብሔርን አገልግሉ አላቸው።
18


እግዚአብሔር ሙሴን “ይህ የፋሲካ ምሽት የእግዚአብሔር መልዐክ የግብፅን በኩር የገደለበት የእናንተን ግን ያለፈበት ነውና አትርሱት” አለው።
19


ከ 430 ዓመታት የባርነት ቆይታ በኋላ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ነጻ ወጡ። እግዚአብሔርም ቀን በደመና አምድ ሌሊት ደግሞ በእሳት አምድ መራቸው።
20



ፈርዖንም
እስራኤላውያንን
አልተዋቸውም።
እግዚአብሔርን
ረሳ። እንደገና
ልቡን አደነደነ።
ሰራዊቱንም
አሰልፎ
አሳደዳቸው።

21



ሙሴም ለሕዝቡ። “እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል”
አላቸው። ሙሴም በባሕሩ ላይ እጁን ዘረጋ።

22



ታላቅ ተዓምር ሆነ።
እግዚአብሔርም ሌሊቱን
ሁሉ ጽኑ የምሥራቅ
ነፋስ አምጥቶ ባሕሩን
አስወገደው፥ ባሕሩንም
አደረቀው፥ ውኃውም
ተከፈለ። ሕዝቡም
በሰላም ተሻገሩ።

23

ግብፃውያንም፥ የፈርዖን ፈረሶችና ሰረገሎች ፈረሰኞቹም ሁሉ፥
እያሳደዱ በኋላቸው ወደ ባሕር መካከል ገቡ። ውኃውም ተመልሶ
በኋላቸው ወደ ባሕር የገቡትን ሰረገሎችን ፈረሰኞችንም
የፈርዖንንም ሠራዊት ሁሉ ከደነ ከእነርሱም
አንድ ስንኳ አልቀረም። ፈርዖንም
እግዚአብሔር ታላቅ እንደሆነ
አየ።



24

ደህና ሰንብት ፈርዖን!

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዘጸአት ምዕ. 4-15

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣
ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን
ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ
ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ
አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ
በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ
ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ
አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር
በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር
ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ
እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16